# አጥፍቶ ጠፊው ኢሣያስ

አገሬ ከስዊድን 2015-02-28

በአዲሷ ኤርትራ  ባህረ ነጋሽ

የሻቢያ ፍቅር  ሳይውል ሳያመሽ

ህዝቡ ተሳደደ  ከስቃይ ሊሸሽ።

 ይቅር መለያየት  አብረን እንኑር

እያለ ሲማፀን  ኢትዮጵያ በፍቅር

አሻፈረኝ ብሎ  ኤርትራ የገባ

ከሀያ አመት በላይ በመሆን ተስፋ አልባ

በነፃዋ ምድር  አነባ ደም እንባ።

ነፃ አወጣሁ ብሎ  የሻቢያው መሪ

በኢሳያስ ዘመን  ጠፋ ፍርፋሪ።

በመንግስቱ ጊዜ  ሰው በላ በሚሉት

ግዳጅ ተጥሎብን  የወር ገቢ በአመት

ወያኔና ሻቢያ  ባመጡት ጦርነት

ኤርትራና ትግራይ  እንዳይኖር ተርቦ

የእናት አገር ጥሪ  ገንዘብ ተሰብስቦ

ዶሮና እንቁላሉ  በግ ፍየሉ ቀርቦ

ጤፉ ጥራጥሬው  የቅባት እህሉ

ዘይቱን ስኳሩን  ሁሌ እንደታደሉ

በጥላቻ መንፈስ  ልባቸው ተሞልቶ

ቅን ልቦናችንን  የሚያስተውል ጠፍቶ

ከወያኔ ጋራ  ተመሳጥሮ በልቶ

ኢትዮጵያ እንድትጠፋ  በመቶ አመት ዝቶ

ታላቅ የራስምታት  የቤት ስራ ሰጥቶ

በቆፈሩት ጉድጓድ  መግባት ተጎትቶ!

ቀድሞ ያሰቡበት  ሳትደርስ ኤርትራ

ሆንግ ኮንግን ሳትሆን  ሙብራትም ሳይበራ

ለአገር ብልፅግና  ፋብሪካ ሳይሰራ

ዩኒቨርስቲውን  ዘግተውት አስመራ

አገር እየመራ  በመዋጮ ገንዘብ

ያውም አስገድዶ  ከስደተኛው ህዝብ

ኤርትራ እየሞተች  ኑዋሪው እየፈራ

ህዝቡ ወጥቶ አየነው  ከሰውነት ተራ።

የመርዝ ብልቃጡ  ኢሳያስ የያዘው

ኢትዮጵያን ሊያጠፋ  ቀድሞ የቀመመው

ህዝቡን አጠፋበት  ለሱም አልጠቀመው።

የናቁት ነጭ ጤፍ  ሽሮና በርበሬ

አሁን ሲናፍቁት  ብርቅ ሲሆን ጥሬ

የማን ነው ጥፋቱ  እስኪ ይታይ ዛሬ?

መነንና ሳባ  የአገር ባህል ልብሱ

ከኢትዮጵያ ወጥቶ  አውሮፓ መድረሱ

ብዙ ተንከራቶ፣ ተመልሶ ሄዶ  ኤርትራው መልበሱ

አማርኛ ዘፈን  ሲያሞቅ ለድግሱ

ኤርትራዊው ከፍቶት  ኢትዮጵያ መፍለሱ

ነፃነት እንዴት ነው?  እናንተው መልሱ።

ለማጥፋት ያሰበው  ኢትዮጵያን እንደ አገር

ጭካኔው አልቀረም  በኤርትራ ምድር

ህዝቡ ተፈርዶበት  ዘላለም ወታደር

ቤት ንብረት እንዳይዝ  ተኝቶ እንዳያድር

ሳዋ ነው የሚያድጉት  ሊጋ ወጣቶቹ

ልጅም ልጅ አልሆነ  ለእናት ለአባቶቹ።

ጨክኖ ቢጠፋ  ኑሮ የመረረው

በጥይት ይቀላል  ሻቢያ ካገኘው

ከሻቢያ ማምለጥ  እድል የገጠመው

ደግሞ በወንድሙ በደሉ ብዙ ነው

ኩላሊት ጉበቱን  በገንዘብ ሲሸጠው።

ብዙ መከራ አይቶ  በደም ተቅበጥብጦ

ሰሀራ በረሀ  በአሸዋ ተውጦ

ወጣት ህፃናቱ  ባህር ውስጥ ሰምጦ

አውሮፓ እንኩዋን ቢደርስ  ራስ ማጥፋት መርጦ

ደመ ከልብ ሲሆን  ባሻው ነፃነቱ

የህፃናት ስቃይ  ማየቱ መስማቱ

ልብ ይነካልና  ሰው በሰውነቱ

አምላከን ተማፀንኩ  ስለህፃናቱ

መላ ቢያበጅለት  ለአጥፍቶ መጥፋቱ።

ገጣሚዋን ማግኘት ከፈለጉ በ  agereamanu@yahoo.se መድረስ ይቻላል።